PDF Complete
Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

# የገቢዎች ሚኒስቴር
## መመሪያ ቁጥር 21/1997
## ስለተጨማሪ እሴት ታክስ አፈፃፀም
## የወጣ መመሪያ

የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ በትክክል ሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ የሚያስችሉ መመሪያዎች ለማውጣት በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የገቢዎች ሚኒስቴር የተለያዩ መመሪያዎችን ያወጣ ቢሆንም አፈፃፀማቸው ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚያወጣው መመሪያ እንደሚወሰን በአዋጁ የተመለከቱ ቀሪ ጉዳዮች ያሉ መሆኑን በመረዳት፣

መመሪያዎቹ በአንድነት ተጠቃለው እንዲወጡ ማድረግ ለታክስ ከፋዩም ሆነ ለታክስ ሰብሳቢው መ/ቤት ሥራ አፈፃፀም አመቺ መሆኑን ስለታመነበት፣

የሚከተለው የተጠቃለለ መመሪያ ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል::

1. <u>አውጪው ባለሥልጣን</u>

   የገቢዎች ሚኒስትር በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል::

2. <u>ትርጓሜ</u>

   1. በዚህ መመሪያ ውስጥ:-

      ሀ/ " ባለሥልጣን " ማለት የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ነው::

      ለ/ " አዋጅ " ማለት የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 ነው::

      ሐ/ " ታክስ " ማለት የተጨማሪ እሴት ታክስ ነው::

   2. በዚህ መመሪያ የተለየ ትርጉም ያልተሰጣቸው ቃላትና ሐረጎች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ::

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Revenues

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.

Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

## 3. የዕቃዎች ስሌሳ አገልግሎት መዋል

1. የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች የገዛ እና ተገቢውን የታክስ ተቀናሽ ያገኘ ወይም የማግኘት መብት ያለው የተመዘገበ ሰው የገዛቸው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ታክስ ለሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ያልዋሉ በሚሆንበት ጊዜ የታክሱ ተቀናሽ ተመላሽ ስለሚደረግበት ሁኔታ በዚህ መመሪያ የተዘረጋው ሥርዓት ተፈፃሚ የሚሆነው ዋጋቸው ከብር 5,000 በላይ ለሚሆን ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ብቻ ይሆናል::

2. ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ሰው የታክስ ተቀናሽ ያገኘባቸውን ወይም ሊያገኝ የሚችልባቸውን ዕቃዎችና አገልግሎቶች ታክስ ለማይከፈልበት ስሌሳ አቅርቦት ያዋለ እንደሆነ፣ የአቅርቦቱ ዋጋ የሚወሰነው ሀX(ለ-ሐ) የሚለውን ስሌት መሠረት በማድረግ ይሆናል::

3. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 2 በተገለፀው ስሌት መሠረት በ«ለ» እና በ«ሐ» መካከል ያለው ልዩነት ከ10% ያልበለጠ በሚሆንበት ጊዜ ለአዋጁ በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (2) አፈፃፀም የዕቃው ወይም የአገልግሎቱ አቅርቦት ለሌሳ አገልግሎት እንደዋለ ተደርጐ አይቆጠርም::

4. በንዑስ አንቀጽ 2 እና 3:-

«ሀ» በማለት የተጠቀሰው ዕቃው ወይም አገልግሎቱ የተገዛበት ዋጋ፣

«ለ» በማለት የተጠቀሰው ባለፈው የ12 ወራት ጊዜ ውስጥ ታክስ ለሚከፈልባቸው የንግድ ሥራ እንቅስቃሴዎች የዋለው ዕቃ ወይም አገልግሎት በመቶኛ ነው:: የ12 ወሩ ጊዜ መቆጠር የሚጠናቀቀው ዕቃው ወይም አገልግሎቱ ታክስ ለማይከፈልበት አቅርቦት ከዋለበት ወር በፊት ባለው ወር መጨረሻ ነው::

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.

Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

«ሐ» ዕቃውን ወይም አገልግሎቱን ለሌላ አቅርቦት ማዋል ከተጀመረ በኋላ እንደገና ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ለማቅረብ የዋለው በመቶኛ ነው::

5. ግምት ውስጥ ስለማይገባ መጠን ልክ በንዑስ አንቀጽ 3 ለተደነገገው አፈፃፀም ዕቃው ወይም አገልግሎቱ ከአንድ በላይ ለሆኑ ታክስ ለማይከፈልባቸው አቅርቦቶች የዋለ እንደሆነ፣ ለእነዚህ አቅርቦቶች የዋለው በሙሉ ለአንድ አቅርቦት እንደዋለ ተቆጥሮ ግምት ውስጥ እንደማይገባ ከተወሰነው መጠን በላይ ከሆነ ይህ መመሪያ ተፈፃሚ ይሆንበታል::

6. ዕቃው ወይም አገልግሎቱ ታክስ ለማይከፈልበት አቅርቦት የዋለ እንደሆነ የዕቃ ወይም የአገልግሎት አቅርቦቱ ተፈፅሟል የሚባለው አቅርቦቱ በተፈፀመበት የሂሳብ ጊዜ መጨረሻ ይሆናል::

## 4. ቀጥታ አቅርቦት

ማናቸውም ሰው የአንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ አቅርቦቶች የተለያዩ ክፍሎች ከታክሱ ነፃ እንዲሆኑ ወይም ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ እንዲሆንባቸው ለማድረግ ሲል በንዑስ ክፍሎች የከፋፈለ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ የሰጠ እንደሆነ የታክሱ ባለሥልጣን እነዚህ አቅርቦቶች ታክስ ከሚከፈልበት ከዋናው ግብይት የተለዩ ራሳቸውን የቻሉ ግብይቶች እንደሆኑ አድርጐ አይወስድም:: በተናጠል የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ የተሰጠባቸው የግብይቱ ክፍሎች አንድ ነጠላ አቅርቦት ተደርገው የሚወሰዱ ሲሆን፣ በአንቀጽ 5(3) መሠረት ራሳቸውን ለቻሉ ግብይቶች የተደረገው ልዩ አስተያየት ተፈፃሚ አይደረግባቸውም:: ስለሆነም ከአቅርቦቱ ጋር በተያያዘ የተሰጠ የትራንስፖርት አገልግሎት ወይም ጥቅም ላይ የዋለ የኤሌክትሪክ ወይም ማናቸውም ሌላ ፍጆታ ታክስ የሚከፈልበት ዕቃ አቅርቦት አንድ ክፍል ሆነው የተጨማሪ እሴት ታክስ ይከፈልባቸዋል::

PDF Complete
Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

5. <u>ምዝገባ በተሠረዘ ጊዜ ተመላሽ ስለሚደረግ ታክስ</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 8 ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ሰው ምዝገባ ሲሰረዝ ቀደም ሲል ተቀናሽ የተደረገው በካፒታል ዕቃዎች ላይ የተከፈለ ታክስ ምዝገባው በተሠረዘ ጊዜ ዕቃው በሚያወጣው ዋጋ ልክ ሽያጭ እንደተከናወነ ተቆጥሮ ታክሱ ሊሰበሰብ እንደሚገባ ተደንግጓል:: የዚህ አፈፃፀም ቀሪው የዕቃው የአገልግሎት ዘመን አካፋይ እና ጠቅላላ የአገልግሎት ዘመኑ ተካፋይ ሆኖ ውጤቱን በዕቃው ዋጋ በመብዛት ይሆናል::

2. በገቢዎች ሚኒስቴር የተለየ መመሪያ ካልወጣ በስተቀር ለአዋጁ አንቀጽ 4(8) አፈፃፀም የካፒታል ዕቃዎች የአገልግሎት ዘመን የሚወሰነው ለስእርጅና ቅናሽ በሚደነገገው የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/2002 አንቀጽ 23 የተመለከተውን የአገልግሎት ዘመን መሠረት በማድረግ ነው::

6. <u>አቅርቦት ተከናወነ የሚባልበት ጊዜ</u>

1. ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ሰው በኪራይ ግዥ ስምምነት (በዱቤ ሽያጭ) የዕቃ አቅርቦት የፈፀመ እንደሆነ፣ በዚህ ዓይነት የተከናወነው አቅርቦት ተፈፅሟል የሚባለው ውሉ ከሚፀናበት ቀን ጀምሮ ይሆናል::

2. ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ሰው ገዥው. የዕቃውን ዋጋ በተወሰኑ ክፍያዎች አስቀድሞ ክፍሎ ሲያጠናቅቅ ዕቃውን በሚረከብበት ውል የአቅርቦት ተግባር ያከናወነ እንደሆነ የዕቃው አቅርቦት ተከናወነ የሚባለው የዕቃው ርክክብ ሲፈፀም ይሆናል:: የዚህ ዓይነቱ የግዥ ውል የተሠረዘ እንደሆነ ሻጩ ገዥው አስቀድሞ የከፈለውን ገንዘብ የሚያስቀር ስለሆነ፣ የግዥው ውል ሲሠረዝ በሻጩ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት እንደተከናወነ እና አቅርቦቱ ሻጩ በገዥው የተከፈለውን ሂሳብ ለማስቀረት የሚያስችለውን መብት ባገኘበት ጊዜ እንደተከናወነ ይቆጠራል::

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

3. በአዋጁ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የታክስ ተቀናሽ የተደረገላቸው ወይም የሚደረግላቸው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ታክስ ለማይከፈልበት አቅርቦት የዋሉ እንደሆነ አቅርቦቱ ታክስ የሚከፈልበት ሆኖ የሚቆጠር ሲሆን፣ አቅርቦቱ ተከናወነ የሚባለው ዕቃዎቹ እና አገልግሎቶቹ ለሌላ ተግባር በዋሉበት ጊዜ ይሆናል::

4. ከግንባታ፣ በግንባታ ሥራ ላይ ከሚደረግ ከፍተኛ ለውጥ፣ ከማምረት ወይም ከሕንፃ ማስፋፋት ወይም ከኢንጂነሪንግ ሥራዎች ጋር ለተያያዙ ተግባራት የዕቃ ወይም የአገልግሎት አቅርቦት የተከናወነ እና ክፍያው የሚፈፀመው በተወሰነ ጊዜ ልዩነት ሲሆን፣ የዕቃው ወይም የአገልግሎቱ አቅርቦት በተከታታይ እንደተፈፀመ ተቆጥሮ ለእያንዳንዱ ተከታታይ አቅርቦት የክፍያ መጠየቂያ በተዘጋጀበት ጊዜ የተከናወነ ሆኖ ይወሰዳል:: ክፍያ የተፈፀመው ወይም መፈፀም ያለበት የክፍያ መጠየቂያው ከመዘጋጀቱ በፊት ከሆነ አቅርቦቱ የክፍያ መጠየቂያው ከመዘጋጀቱ በፊት ሊከናወን ይችላል:: ይህ በሚሆንበት ጊዜ አቅርቦቱ ተከናወነ የሚባለው ክፍያ የሚፈፀምበት ጊዜ ሲደርስ ወይም ክፍያው ሲፈፀም ከሁለቱ ቀዳሚ በሆነው ጊዜ ይሆናል::

7. <u>የአቅርቦት ዋጋ</u>

በገዥ እና በሻጭ መካከል የተደረገው ገዥው የዕቃውን ዋጋ በተወሰኑ ክፍያዎች አስቀድሞ ከፍሎ ሲያጠናቅቅ ዕቃውን የሚረከብበት ውል የተሠረዘ እና ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበው ሰው ገዥው አስቀድሞ የከፈለውን ገንዘብ ያስቀረ እንደሆነ፣ ውሉ ሲሠረዝ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት እንደተፈፀመ እና የተመዘገበው ሰው ያስቀረው ገንዘብ ለአቅርቦቱ የተከፈለው ዋጋ እንደሆነ ይቆጠራል::

8. <u>የታክስ ማቀናነስ አፈፃፀም</u>

1. ታክስ ለሚከፈልባቸው ግብይቶች እንዲውሉ ወደአገር በገቡ ወይም በአገር ውስጥ በተገዙ ዕቃዎች ላይ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሙሉ በሙሉ ተቀናሽ ይደረጋል:: ሆኖም ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ ለተደረጉ ግብይቶች እንዲውሉ ወደአገር ውስጥ በገቡ ወይም በአገር ውስጥ በተገዙ ዕቃዎች ላይ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ በማናቸውም ሁኔታ ተቀናሽ አይደረግም::

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

2. ስተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ሰው ወደአገር ያስገባቸው ወይም በአገር ውስጥ የገዛቸው ዕቃዎች በከፊል ታክስ ለሚከፈልባቸው በከፊል ደግሞ ለማይከፈልባቸው ግብይቶች የዋሉ እንደሆነ የታክስ ተቀናሽ ተፈፃሚ የሚሆነው በዚህ መመሪያ በተመለከተው የማከፋፈያ ዘዴ መሠረት ይሆናል::

## 9. የማከፋፈል መርሆዎች

1. ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ሁኔታዎች መሠረት ካልሆነ በስተቀር ስተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ሰው የማከፋፈል ዘዴን ሥራ ላይ የሚያውለው የአቅርቦቶቹን ጠቅላላ ዋጋ መሠረት በማድረግ ይሆናል:: ሆኖም:-

ሀ/ ባንክ ወይም ከታክሱ ነፃ የሆኑትን የፋይናንስ አገልግሎቶች የሚሰጥ ሌላ አቅራቢ የፋይናንስ እንቅስቃሴዎችን ከማገዝ ጋር በተያያዘ የሚሰጠውን አገልግሎት ዋጋ ስሌት ሲያከናውን የተከፈለውን ወለድ እና ከወለድ የተገኘውን ገቢ መቀነስ አለበት::

ለ/ የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ታክስ የሚከፈልበትን የሎተሪ ግብይት ዋጋ ስሌት ሲያከናውን በጥሬ ገንዘብ የተሰጡ ሽልማቶችን እና ከሎተሪ ሽያጭ የተገኘውን ገቢ መቀነስ አለበት::

2. የተመዘገበ ሰው የሚገዛቸውን ዕቃዎች ሲያውል ያቀደበትን ተግባር መሠረት በማድረግ በትክክል የሚመለከተውን እና ተገቢ እና ምክንያታዊ የሆነውን እንዲሁም በሰነድ ሊደገፍ የሚችለውን የማከፋፈል ዘዴ መምረጥ አለበት::

3. በአዋጁ አንቀጽ 21፣ 2(ሀ) እና 2(ለ) በተደነገገው መሠረት የታክስ ተቀናሹን ሙሉ በሙሉ ታክስ ለሚከፈልበት ግብይት ወይም ከታክሱ ነፃ ለሆነ ግብይት ለማዋል የሚፈልግ የተመዘገበ ሰው ወደአገር የሚገባው ወይም በአገር ውስጥ የሚገዛው ዕቃ የሚውልበትን ዓላማ በሚመለከት በምክንያት ላይ የተደገፈ ግምት ሊኖረው ይገባል:: ይህ ግምት በምክንያት ላይ የተደገፈ ግምት እንዲሆን ለማድረግ የሚያግዙ እስከሆነ ድረስ ያለፉ ልምዶችን ወይም የቅርብ ጊዜ ልምዶችን መሠረት ሊያደርግ ይችላል::



285

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.

Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

## 10. የማከፋፈያ ቀመር

1. ለአዋጁ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 2(ሐ) አፈፃፀም በከፊል ታክስ ለሚከፈልበት ግብይት በከፊል ደግሞ ከታክሱ ነፃ ለሆኑ ግብይቶች በዋሉ ወደአገር በገቡና በአገር ውስጥ በተገዙ ላይ የተከፈለውን ታክስ የተመዘገበው ሰው ከዚህ በታች በተመለከተው ቀመር መሠረት አስልቶ ማቅረብ አለበት::

   ተ= ሀ X ለ/ሐ

   ለዚህ ስሌት አፈፃፀም፣

   «ተ» ተቀናሽ (ክሬዲት) ሲደረግ የሚገባ ታክስ ልክ

   «ሀ» በከፊል ታክስ በሚከፈልበት በከፊል ደግሞ ከታክሱ ነፃ በሆኑ ግዥዎች ላይ የተከፈለ ጠቅላላ ተጨማሪ እሴት ታክስ፣

   «ለ» የተመዘገበው ሰው በሂሳብ ዘመኑ ወስጥ ያከናወነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ዋጋ ነው::

   «ሐ» የ ተመዘገበው ሰው በሂሳብ ዘመኑ ውስጥ ያከናወናቸው ጠቅላላ አቅርቦቶች ዋጋ ነው::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተመለከተው ለ/ሐ ቀመር መሠረት ሲሰላ የሚገኘው ውጤት ከ0.90 በላይ ከሆነ በፎርሙላው ፊደል «ሀ» የተመለከተው ታክስ ሙሉ በሙሉ ተቀናሽ ይደረጋል::

3. የተመዘገበው ሰው የሚያከናውናቸው ታክስ የሚከፈልባቸው እና ከታክሱ ነፃ የሆኑ ግብይቶች የማከፋፈል ስሌት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተመለከተው ቀመር መሠረት ቢከናወን የተፈለገውን ውጤት የማያስገኝ ከሆነ የታክሱ ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ በሂሳብ ዘመኑ ውስጥ ተቀናሽ የሚደረገው ታክስ ተገቢ መስሎ በታየው ሌላ ስሌት እንዲከናወን ሊያደርግ ይችላል::

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

4. የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ ይህንን ሥልጣኑን ሥራ ላይ በሚያውልበት ጊዜ፣ ከሌሎች መካከል ለጠቅላላው የሥራ እንቅስቃሴ ከዋለው ጊዜ ውስጥ ታክስ ለሚከፈልበት ግብይት የዋለውን ጊዜ መሠረት በማድረግ፣ ወይም ሠራተኞች ለጠቅላላው የሥራ እንቅስቃሴ እና ታክስ ለሚከፈልበት የሥራ እንቅስቃሴ ያዋሉትን በማመዛዘን፣ የጠቅላላውን የሥራ እንቅስቃሴ ቁጥር ታክስ ከሚከፈልበት ግብይት ቁጥር ጋር በማመዛዘን፣ ከጠቅላላው የሥራ እንቅስቃሴ የተገኘውን ትርጽ ታክስ ከሚከፈልበት ግብይት ከተገኘው ትርፍ ጋር በማመዛዘን፣ ወይም ለጠቅላላው የሥራ እንቅስቃሴ ጥቅም ላይ ከዋለው ቦታ፣ ታክስ ለሚከፈልበት ግብይት የዋለውን ቦታ በማመዛዘን የታክስ ማቀናነሱን ሊፈቅድ ይችላል።

11. <u>ሎተሪዎች</u>

1. ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም፡-

ሀ/ «የሎተሪ ድርጅት» ማለት በአዋጅ ቁጥር 210/1973 የተቋቋመው የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ድርጅት እና የሎተሪ ግብይት እንዲያከናውን የተፈቀደለት ሰው ነው።

ለ/ «የሎተሪ ግብይት» ማለት በብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ድርጅት ወይም ከብሔራዊ ሎተሪ አስታዳደር ድርጅት ፈቃድ በተሰጠው ሰው የሚካሄድ ከሎተሪ፣ ከቢንጐ፣ ከካዚኖ እና መሰል የዕድል መከራ ሥራ እንቅስቃሴ ጋር በቀጥታ የተያያዘ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ነው።

2. በዚህ መመሪያ በተለየ ሁኔታ እንዲፈፀም ካልተወሰነ በስተቀር የአዋጁ ድንጋጌዎች በሙሉ በሎተሪ ድርጅት ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

3. የአዋጁ አንቀጽ 20 የተመዘገበ ሰው በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ ሲከፍለው የሚገባው ታክስ የሚሠሳባቸውን አጠቃሳይ ደንቦች ይደነግጋል። በዚህ አንቀጽ መሠረት ተከፋይ የሚሆነው በአንቀጽ 7 መሠረት ታክስ በሚከፈልበት



Federal Democratic ... Ministry of Revenue
287

ግብይት ላይ ሲከፈል ከሚገባው ታክስ፣ በአዋጁ አንቀጽ 21 መሠረት የተፈቀደ ተቀናሽ ከተደረገ በኋላ የሚቀረው ታክስ ነው:: ይህ የአዋጁ ድንጋጌ የሎተሪ ግብይትን ሪፖርት ማድረግን ሳይጨምር የሎተሪ ድርጅት በሚያከናውናቸው ታክስ የሚከፈልባቸው ግብይቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል::

4. የሎተሪ ድርጅት ከሎተሪ ቲኬቶች ሽያጭ ከሚገኘው ገቢ ለዕጣ አሸናፊዎች ተከፍሎ የሚቀረውን በሚያስገኝ የትርፍ ህዳግ ሥርዓት የሚሠራ ነው:: በሎተሪ ተሳታፊ ለመሆን ማናቸውም ሰው የሚከፍለው ገንዘብ አገልግሎት ለማግኘት እንደተከፈለ ክፍያ ይቆጠራል::

5. ለሪፖርት አቀራረብ ሲባል፣ የሎተሪ ድርጅት በሎተሪ ግብይት ላይ ሲከፈል የሚገባውን ታክስ ሪፖርት የሚያደርገው ሀ(ለ-ሐ) የሚለውን ቀመር በመጠ ቀም ሲሆን፣

«ሀ» የታክስ ክፍልፋይ የሆነው 15/115፣

«ለ» የሎተሪ ድርጅት በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ ባከናወነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ታክስ ሲከፈልበት የሚገባው የገንዘብ መጠን ድምር፣

«ሐ» የ ሎተሪ ድርጅት በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ ለዕጣ አሸናፊዎች የከፈለው ገንዘብ ድምር ነው::

6. በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ ከተከናወነ የሎተሪ ግብይት ታክስ ሲከፈልበት የሚገባው የገንዘብ መጠን በሂሳብ ጊዜው ውስጥ ለሎተሪ አዟሪዎች፣ ለወኪሎች እና ለተጠቃሚዎች ከተፈፀመ ሎተሪ ሽያጭ ከተገኘ ገንዘብ ላይ፣ ያልተሸጡ የሎተሪ ቲኬቶች በመመለሳቸው በሂሳብ ጊዜው ውስጥ ለሎተሪ አዟሪዎች እና ለወኪሎች መልሶ የተከፈለ ሂሳብ ሲቀነስ የሚቀረው ነው::

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 በተመለከተው ቀመር መሠረት ለዕጣ አሸናፊዎች በጥሬ ገንዘብ ከተከፈለው በስተቀር የሎተሪ ድርጅት በአዋጁ አንቀጽ 21 በተመለከተው የሂሳብ ጊዜ ውስጥ በአዋጁ አንቀጽ 21 በተፈቀደው መጠን የታክስ ቅናሽ ሲያገኝ ይችላል::

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

8. የሎተሪ ድርጅት በአዋጁ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የታክስ ተቀናሽን ከፋፍሎ እንዲያቀርብ የሚጠበቅ ሲሆን፣ በአዋጁ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 2/ሐ/ ስተመለከተው ቀመር አፈፃፀም ታክስ የሚከፈልበት የሎተሪ ግብይት የሚሆነው በንዑስ አንቀጽ 5 የተመለከተው (ሰ-ሐ) ቀመር 100/115 ይሆናል::

9. የመንግሥት መ/ቤቶች የሎተሪ ድርጅትን የሚያስከፍሉት የዕቃና አገልግሎት ክፍያ ወይም ሌላ ተመሳሳይ ክፍያ ተጨማሪ እሴት ታክስ ካልተከፈለበት እና የመንግሥት መ/ቤቱ ታክሱን ወይም ክፍያውን የሚያጠቃልል የታክስ ደረሰኝ ካልሰጠ በስተቀር የታክስ ቅናሽ የሚገኝበት አይሆንም::

10. በሎተሪ ዕጣው አሸናፊ ወይም አሸናፊዎች የሌሉ እንደሆነ እና ለዕጣ አሸናፊ የተዘጋጀው ሽልማት ወደፊት ለሚወጣ ዕጣ እንዲውል የተደረገ እንደሆነ፣ ለወደፊት የሚወጣው ዕጣ ካልወጣ እና ሽልማቱ ለአሸናፊዎች ካልተሰጠ በስተቀር ለወደፊት ለሚወጣ ዕጣ እንዲውል ከተቀመጠው ገንዘብ ጋር የተያያዘው ሂሳብ ወይም ዕዳ በዚህ መመሪያ ተራ ቁጥር 5 መሠረት በሎተሪ እንቅስቃሴው ላይ የሚከፈለው ታክስ በሚሠላበት ጊዜ ከግምት ውስጥ የሚገባ አይሆንም::

11. የሎተሪው ድርጅት በሎተሪ ዕጣ አሸናፊ ለሆኑ የዓይነት ሽልማት የሚሰጥ ከሆነ፣ በዚህ መመሪያ ተራ ቁጥር 5 መሠረት በሎተሪ እንቅስቃሴ ላይ ሊከፈል የሚገባው ታክስ በሚሠላበት ጊዜ በዓይነት የሚሰጠው ሽልማት ዋጋ ከግምት ውስጥ አይገባም::

12. የሎተሪው ድርጅት በዓይነት የሚሰጠውን ሽልማት እንደግብአት በመውሰድ በአዋጁ አንቀጽ 21 በተደነገገው መሠረት ሽልማቱን በሚገዛበት ጊዜ የከፈለው ተጨማሪ እሴት ታክስ ተቀናሽ እንዲሆንለት መጠየቅ ይችላል::

13. በአዋጁ አንቀጽ 21 ተቀናሽ ስለማይደረጉ ወጪዎች የተደነገገው ለዕጣ አሸናፊዎች በዓይነት የሚሰጡ ሽልማቶችን በሚመለከት ተፈፃሚ ይሆናል::



06289

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

360

## 12. የጉዞ ወኪሎች እና የአስጐብኚዎች አገልግሎት

1. ነዋሪ የሆነ የጉዞ ወኪል ወይም አስጐብኚ ድርጅት የሚባለው በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ እና በኢትዮጵያ ውስጥ በጉዞ ወኪልነት ወይም በአስጐብኚነት የሥራ እንቅስቃሴዎች ላይ የተሠማራ ወይም በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነና በቋሚነት በሚሠራ ድርጅት አማካኝነት በኢትዮጵያ ውስጥ በጉዞ ወኪልነት ወይም በአስጐብኚነት የሥራ እንቅስቃሴዎች ላይ የተሠማራ ሰው ነው።

2. ነዋሪ የሆነ የጉዞ ወኪል በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆነ ሰው ከኢትዮጵያ ውጪ የሚደረጉ ጉዞዎችን ያመቻቸ እንደሆነ ከኢትዮጵያ ውጪ ለሚደረጉ ጉዞዎች የተደረገው ክፍያ /የዓለም ዐቀፍ የአየር ትራንስፖርት፣ ከኢትዮጵያ ውጪ የሚደረግ የሆቴል እና የምግብ አገልግሎትን ጨምሮ/ በአዋጁ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ/ እና 2/ለ/ መሠረት ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ ይደረግበታል። የጉዞ ወኪሉ ጉዞዎቹን በማመቻቸት ለሚሰጠው አገልግሎት የሚከፈለው ክፍያ ወይም ኮሚሽን በኢትዮጵያ ውስጥ የተከናወነ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ነው።

3. አስጐብኚ ድርጅቱ የአገልግሎቱ ቀጥታ አቅራቢ ሲሆንና አገልግሎቱም የተጨማሪ እሴት ታክስ ሊከፈልበት የሚገባ ከሆነ ታክሱን ሰብስቦ ገቢ ያደርጋል። ሆኖም አገልግሎቱ በሦስተኛ ወገን የሚሰጥ ከሆነ አስጐብኚው ድርጅት የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰብስቦ ገቢ የሚያደርገው በኮሚሽኑ ድርሻ ላይ ብቻ ይሆናል።

4. የጉዞ ወኪሉ ደንበኞችን ከቦታ ወደ ቦታ እንዲያዘዋውር የመደበው ሠራተኛ ያገኘው የሆቴልና የምግብ አገልግሎት የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ በአዋጁ አንቀጽ 21 መሠረት ተቀናሽ አይደረግም።

5. ነዋሪ የሆነ የጉዞ ወኪል ወይም አስጐብኚ ወይም በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ የጉዞ ወኪል ወይም አስጐብኚ የኢትዮጵያ ወኪል በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆነ ሰው የአገር ውስጥ ጉብኝት ያመቻቸ እንደሆነ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ የሚደረግባቸው እንደዓለም ዐቀፍ ትራንስፖርት ካሉ አገልግሎቶች በስተቀር ከጉብኝቱ ጋር በተያያዘ የሚሰጡ አገልግሎቶች ታክስ የሚከፈልባቸው ይሆናል።



የ8-6 290

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.

Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

6. በኢትዮጵያ ነዋሪ ባልሆነ የጉዞ ወኪል ወይም አስጉብኚ ስም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚሰጡ አገልግሎቶች በአዋጁ አንቀጽ 7 ወይም 8 መሠረት ከታክሱ ነፃ የተደረጉ ወይም ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ የሚደረግባቸው ካልሆኑ በስተቀር ታክስ የሚከፈልባቸው ግብይቶች ናቸው።

7. በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው /እንደ ወጭ አገር አስጉብኚ ድርጅት ወይም የጉዞ ወኪል ያለ/ በኢትዮጵያ ነዋሪ ሳልሆነ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚደረግን ጉብኝት የሚጨምር /እንደ አደን ጉዞ የመሳሰሉ/ ጉዞ ያመቻቸ እንደሆነ በአገር ውስጥ የሚሰጠው አገልግሎት ታክስ ይከፈልበታል።

8. በተራ ቁጥር 7 ከተመለከተው ጉዞ ጋር በተያያዘ በውጭ አገር ያለው ሰው ከኢትዮጵያ ወጪ ለሚሰጠው አገልግሎት የሚከፈል ኮሚሽን ወይም ለዓለም ዐቀፍ ትራንስፖርት የሚከፈል ክፍያ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ ይደረግበታል። በውጭ አገር ያለ የጉዞ ወኪል በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚሰጥ የጉዞ አገልግሎት ጋር በተያያዘ የሚያገኘው ኮሚሽን፣ በኢትዮጵያ ነዋሪ ሳልሆነ እና አገልግሎቱ በተሰጠበት ጊዜ ከኢትዮጵያ ወጪ ለሚገኝ ሰው በተሰጠ አገልግሎት የተገኘ በመሆኑ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ ይደረግበታል።

9. በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆነ ሰው ወኪል ሆኖ የሚሠራ በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ የጉዞ ወኪል ወይም አስጉብኚ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚደረግን ጉብኝት ያመቻቸ እና ለዚህም አገልግሎቱ ኮሚሽን የተከፈለው እንደሆነ በኢትዮጵያ የሚገኘው የተመዘገበ ሰው ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ ከሚደረግበት የሥራ እንቅስቃሴ ለምሳሌ በውጭ አገር ላለው ወኪል ከሚከፈል ኮሚሽን እና ከዓለም ዐቀፍ ትራንስፖርት አገልግሎት ወጪ በስተቀር በጉዞው ወጪ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ መክፈል አለበት።

13. <u>ያገለገሉ ዕቃዎች ሽያጭ</u>

1. ያገለገሉ ዕቃዎችን በመሸጥ ተግባር ላይ የተሠማራ የተመዘገበ ሰው እነዚህን ዕቃዎች የገዛው ከተመዘገበ ወይም ካልተመዘገበ ሰው ሊሆን ይችላል። ከተመዘገበ ሰው በተገዙ ዕቃዎች ላይ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ



291

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

በአዋጁ አንቀጽ 21 መሠረት ተቀናሽ የሚደረግ ሲሆን፣ ካልተመዘገበ ሰው በተገዛ ዕቃ ላይ የተከፈለ ታክስ ግን ተቀናሽ አይደረግም።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3-6 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ያገለገሉ ዕቃዎች በመሸጥ ተግባር ላይ የተሠማራ የተመዘገበ ሰው በአዋጁ አንቀጽ 21 መሠረት የታክስ ማቀናነስ እንዲደረግለት ሊጠይቅ የሚችለው በሚከተለው ሁኔታ ነው፣

ሀ/ በአዋጁ በተደነገገው መሠረት ዕቃዎቹ በ15% የማስከፈያ ልክ ታክስ የሚከፈልባቸው ከሆነ የተመዘገበው ሰው በሂሳብ ጊዜው ውስጥ ከተመዘገበ ሰው ታክስ በሚከፈልበት ግብይት በኢትዮጵያ ውስጥ የገዛቸው ታክስ ለሚከፈልበት ግብይት የሚውሉ ያገለገሉ ዕቃዎች 15/115 በሆነ የታክስ ክፍልፋይ ሲሰላ ከሚደረስበት ሂሳብ ጋር እኩል ሊሆን የሚችል ከሚከተሉት አነስተኛው የገንዘብ መጠን፣

i ለዕቃው ከተከፈለው የገንዘብ መጠን፣ ወይም
ii ታክስን ጨምሮ ከዕቃው የገበያ ዋጋ፣

ለ/ ግንኙነት ላለው ሰው በሚቀርቡት ዕቃዎች ላይ ሊከፈል ከሚገባው ታክስ ያልበለጠ እስከሆነ ድረስ በአዋጁ በተደነገገው መሠረት ዕቃዎቹ በ15% የማስከፈያ ልክ ታክስ የሚፈልባቸው ከሆነ የተመዘገበው ሰው በሂሳብ ጊዜው ውስጥ ከተመዘገበ ግንኙነት ያለው ሰው ታክስ በሚከፈልበት ግብይት በኢትዮጵያ ውስጥ የገዛቸው ታክስ ለሚከፈልበት ግብይት የሚውሉ ዕቃዎች 15/115 በሆነ የታክስ ክፍልፋይ ሲሰላ ከሚደረስበት ሂሳብ ጋር እኩል ሊሆን የሚችል ከሚከተሉት አነስተኛ የገንዘብ መጠን፣

i ለዕቃው ከተከፈለው የገንዘብ መጠን፣ ወይም
ii ታክስን ጨምሮ ከዕቃው የገበያ ዋጋ፣

ሐ/ በውሉ መሠረት ሳልፈፀመው የዱቤ ግዥ በቀረበው ዕቃ ላይ ሊከፈል ከሚገባው ታክስ ያልበለጠ እስከሆነ ድረስ በአዋጁ በተደነገገው

Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Revenue

PDF Complete
Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

መሠረት ዕቃው በ15% የማስከፈያ ልክ ታክስ የሚከፈልበት ከሆነ የተመዘገበው ሰው በውሉ መሠረት ካልፈፀመ የዱቤ ገዥ በሂሳብ ጊዜው ውስጥ ታክስ በሚከፈልበት ግብይት መልሶ ስተረከበው ታክስ ስሚከፈልበት ግብይት ስሚውል ያገለገለ ዕቃ ከዋጋው 15/115 ከሆነ የታክስ ክፍልፋይ ጋር እኩል በሆነ የገንዘብ መጠን፣

መ/ የመድን ዋስትና ስተሰጠው ሰው በሚቀርበው ዕቃ ላይ ከሚከፈለው ታክስ ያልበለጠ እስከሆነ ድረስ የተመዘገበ የኢንሹራንስ ድርጅት ታክስ በማይከፈልበት ግብይት የመድን ዋስትና ከተሰጠው ሰው በሂሳብ ጊዜው ውስጥ የተረከበው ያገለገለ ዕቃ፣

i በካሣ ክፍያ ጥያቄ ምክንያት የተገኘ ከሆነ፣

ii በአዋጁ በተደነገገው መሠረት በ15% የማስከፈያ ልክ ታክስ የሚከፈልበት ከሆነ፣

iii ታክስ በሚከፈልበት ግብይት መልሶ ስመሸጥ የሚውል ከሆነ፣

የዕቃው ዋጋ 15/115 ከሆነ የታክስ ክፍልፋይ ጋር እኩል በሆነ የገንዘብ መጠን፣

3. ይህ መመሪያ ስኪራይ በሚውሉ ያገለገሉ ዕቃዎች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም::

4. የተመዘገበ ሰው ታክስ ስሚከፈልባቸው ግብይቶች እንዲውል የገዛውን እና በአዋጁ አንቀጽ 21 መሠረት የታክስ ማቀናነስ ያገኘበትን ንብረት የሸጠ እንደሆነ ግብይቱ ታክስ የሚከፈልበት ይሆናል:: ሆኖም የተመዘገበ ሰው የተጨማሪ እሴት ታክስ በሚከፈልበት ግብይት በገዛው ንብረት ላይ በአዋጁ አንቀጽ 21 ድንጋጌ ምክንያት የታክስ ማቀናነስ ያላገኘ ከሆነ ይህ ንብረት ሲሸጥ ግብይቱ ታክስ የሚከፈልበት አይሆንም::

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Revenues

5. ያገለገሉ ዕቃዎች የሚባሉት የዕቃዎቹ ባለቤት በነበረ ሰው አዲስ ዕቃ ሆነው እንዲቆጠሩ በማያስችል ሁኔታ ጥቅም ላይ የዋሉ፣ ስተለዩ አገልግሎት በሚውል መልክ የተዘጋጁ ወይም በመጋዘን ተቀምጠው የቆዩትን ጨምሮ በሌላ ባለቤት ሥር የነበሩ፣ የተለበሱ ወይም ጥቅም ላይ የዋሉ ዕቃዎች ናቸው::

6. የሚከተሉት ያገለገሉ ዕቃዎች አይባሉም:-

ሀ/ ከከበረ ብረት የተሠሩ ያገለገሉ ዕቃዎች ወይም

ለ/ ከወርቅ፣ ከብር፣ ከፕላቲኒየም ወይም በሚያስፈልገው ጥራት የተሠራ ከሆነ የከበረ ብረት ከሚሆን ከማናቸውም ሌላ ዕቃ የተመረተ ወይም የተሠራ ያገለገለ ዕቃ፣

ሐ/ የቁም ከብት፣

7. በዚህ መመሪያ መሠረት የታክስ ማቀናነስ ሊፈቀድ የሚችለው፣ የታክስ ቅናሽ እንዲደረግለት የሚጠይቀው የተመዘገበ ሰው፣ አቅራቢው ለተመዘገበው ሰው የሸጣቸውን ዕቃዎች የገዛው አዋጁ ከፀናበት ቀን በኋላ መሆኑን እና ታክሱ መከፈሉን የሚያረጋግጡ የፅሑፍ መረጃዎችን እንዲሁም በታክሱ ባለሥልጣን ወይም በዚህ መመሪያ እንዲቀርቡ የሚጠየቁ መረጃዎችን ካቀረበ ብቻ ነው::

8. የታክሱ ባለሥልጣን በዚህ መመሪያ መሠረት የሚቀርበውን የታክስ ማቀናነስ ጥያቄ የሚደግፉ መረጃዎች ላይ ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ የታክስ ማቀናነስ ጥያቄ ያቀረበው የተመዘገበ ሰው የታክስ ተቀናሽ የማግኘት መብት ያለው መሆኑን የማስረዳት ኃላፊነት ይኖርበታል::

9. የተዘገበው ሰው በዚህ መመሪያ መሠረት የታክስ ማቀናነስ እንዲፈቀድ የሚቀርበውን ጥያቄ የሚደግፉ፣ ያገለገሉ ዕቃዎች ያቀረበለትን ሰው ስም እና አድራሻ፣ የአቅራቢውን የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር (የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የሌለው ከሆነ የመታወቂያ ቁጥሩን)፣ ዕቃዎቹ የተገዙበትን ቀን፣ የዕቃዎቹን ዝርዝር መግለጫ፣ የዕቃዎቹን ብዛት ወይም መጠን

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

ጨምር የግብይቱን ዝርዝር አፈፃፀም የሚያሳዩ መረጃዎችን መያዝ ያለበት ሲሆን፣ ከዚህም በተጨማሪ፣

ሀ/ በአንቀጽ 5(2)(ሀ) ለተገለፀው ግብይት ለዕቃው የተከፈለውን ዋጋ እና ትክክለኛውን የገበያ ዋጋ፣

ለ/ በአንቀጽ 5(2)(ለ) ለተገለፀው ግብይት የተከፈለውን ታክስ ልክ፣ የዕቃዎቹን ትክክለኛ የገበያ ዋጋ፣ እና ግንኙነት ባለው ሰው የተከፈለውን ታክስ ልክ፣

ሐ/ በአንቀጽ 5(2)(ሐ) ለተገለፀው ግብይት መልሶ የተረከባቸውን ዕቃዎች ዋጋ እና በውል በገባው ግዴታ መሠረት ያልፈፀመው የዱቤ ገዥ ዕቃዎቹን ሲገዛ የከፈለውን ታክስ፣

መ/ በአንቀጽ 5(2)(መ) ለተገለፀው ግብይት በመድን ካሣው ጥያቄ ምክንያት የተረከባቸውን ዕቃዎች ዋጋ እና የመድን ዋስትናው ተጠቃሚ ዕቃዎቹን ሲገዛ የከፈለውን ታክስ፣

10. የተከፈለው የገንዘብ መጠን ወይም የገዛቸው ዕቃዎች ዋጋ ከብር 50 የማይበልጥና ከሆነ የተመዘገበው ሰው ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን መረጃዎች እንዲይዝ አይገደድም::

11. በንዑስ አንቀጽ 8 መሠረት የሚቀርቡ መረጃዎች የአቅራቢው ፊርማ የሠፈረባቸው መሆን አለባቸው::

## 14. የኮሚሽን ወኪሎች እና ደላሎች

1. የኮሚሽን ወኪሎች እና ደላሎች ለሚሰጡት አገልግሎት የሚከፈላቸው ኮሚሽን፣ የማበረታቻ ክፍያ፣ ቦነስ ወይም ሌላ ማናቸውም ክፍያ ታክስ በሚከፈልበት ግብይት የተገኘ ክፍያ ተደርጐ ይወሰዳል:: የኮሚሽን ወኪሉ ወይም ደላላው ራሱን ችሎ የሚሠራ ወይም በተለመደው የወካይ እና

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

የተወካይ ግንኙነት በወካዩ ሥር ሆኖ የሚሠራ ቢሆንም የአዋጁ ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

2. የኮሚሽን ወኪል ወይም ደላላ አገልግሎቱን የሰጠበት ጊዜ ነው ተብሎ የሚወሰደው በአዋጁ አንቀጽ 11 የተደነገገው ጊዜ ነው፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 11 በተደነገገው መሠረት ክፍያ በተፈፀመ ወይም አገልግሎቱ በተሰጠበት ጊዜ የኮሚሽን አገልግሎት መስጠቱን በተፋጠነ ሁኔታ የማስታወቅ ግዴታ ካልኖረ በስተቀር የኮሚሽን ወኪሎች ወይም ደላሎች የሚያከናውኑት ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ሪፖርት የሚደረገው በሂሳብ ጊዜው ውስጥ ይሆናል፡፡

3. የተመዘገበ የኮሚሽን ወኪል ወይም ደላላ፣ ኮሚሽን፣ የማበረታቻ ክፍያ፣ ቦነስ ወይም ከአገልግሎቱ ጋር የተያያዘ ሌላ ማናቸውም ክፍያ የተቀበለ እንደሆነ፣ የኮሚሽን ወኪሉ ወይም ደላላው ለአገልግሎቱ ለተቀበለው ክፍያ የታክስ ደረሰኝ መስጠት አለበት፡፡

4. የተመዘገበ የኮሚሽን ወኪል ወይም ደላላ በአዋጁ አንቀጽ 21 በተፈቀደው መሠረት ታክስ ለሚከፈልበት ግብይት እንዲውሉ በፈፀማቸው ግዥዎች ላይ የከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ተቀናሽ ይደረግለታል፡፡

5. የኮሚሽን ወኪሉ ወይም ደላላው በተቀበለው ኮሚሽን ወይም ሌላ ማናቸውም ክፍያ ላይ ማስተካከያ (ለውጥ) የተደረገ እንደሆነ የኮሚሽን ወኪሉ ወይም ደላላው በአዋጁ አንቀጽ 13 በተደነገገው መሠረት የታክስ ዴቢት ወይም ክሬዲት ሰነድ መስጠት ይችላል፡፡

## 15. <u>የፖስታ አገልግሎት</u>

ከኢትዮጵያ ወደውጭ አገር ለሚላኩ ፖስታዎች እና ሌሎች ዕቃዎች የሚከፈል ዋጋ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ የሚደረግበት ሲሆን፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚሰጥ የፖስታ አገልግሎት ከውጭ አገር የሚገኝ ገቢ መሠረት የሚያደርገው ከኢትዮጵያ ወደውጭ ለሚላክ ወይም ወደኢትዮጵያ ለሚላክ ዓለም ዐቀፍ የፖስታ አገልግሎት ሕብረት የሚወስነው የማስታረቂያ ሂሳብ ነው፡፡

ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሚኒስቴር
Democratic Republic
Ministry of Revenues

296

16. <u>ከተበዳሪዎች የሚፈለግን ዕዳ ለመሰብሰብ የፋይናንስ ተቋማት ስለሚሸጡት የባለዕዳ ንብረት</u>

1. ለፋይናንስ አገልግሎት የተሰጠው ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት የፋይናንስ ተቋማት የሚሸጡትን በዋስትና የያዙትን የባለዕዳ ንብረት አይጨምርም፡፡

2. የፋይናንስ ተቋም ወይም ከታክሱ ነፃ የሆኑትን የፋይናንስ አገልግሎቶች የሚሰጥ ሌላ ድርጅት በዋስትና የያዛቸውን የባለዕዳ ንብረቶች የሸጠ እንደሆነ ግብይቱ ታክስ የሚከፈልበት ይሆናል፡፡

17. <u>ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ማከናወን የሚጀምር ታክስ ከፋይ በእጁ በሚገኙ ዕቃዎች ላይ የከፈለው ታክስ ስለሚካካስበት ሁኔታ</u>

1. የተመዘገበ ሰው ታክስ ለሚከፈልባቸው ግብይቶች እንዲውሉ በገዛቸው ዕቃዎች ላይ የከፈለው ታክስ ተቀናሽ ሲደረግለት የሚገባ መሆኑ የተደነገገ በመሆኑ ታክስ የሚከፈልበትን ግብይት ከመጀመር ጋር በተያያዘ የሚከናወነው ተግባር ታክስ የሚከፈልበት ግብይት አካል ይሆናል፡፡ ስለሆነም ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ሰው የታክስ ደረሰኝ ወይም የጉምሩክ ዲክላራሲዮን የሚያቀርብ ከሆነ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ለመጀመር ከሚደረግ ዝግጅት ጋር በተያያዘ የተከፈለ ተጨማሪ እሴት ታክስ በአዋጁ በተደነገገው መሠረት ተቀናሽ የሚደረግ ይሆናል፡፡

2. የተመዘገበው ሰው ተቀናሽ ሲደረግለት የሚገባው ሂሳብ ከሰበሰበው ታክስ የበለጠ እንደሆነ የታክሱ ባለሥልጣን የሂሳቡን ትክክለኛነት ካረጋገጠ በብልጫ የታየው ሂሳብ ተመላሽ እንዲሆን ሊፈቅድ ይችላል፡፡

3. የተመዘገበው ሰው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ከመጀመሩ በፊት የገዛቸውን የካፒታል ዕቃዎች የተቀናሽ ጥያቄ ከሚያቀርብበት የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ማቅረቢያ የሂሳብ ጊዜ በፊት ታክስ ለሚከፈልበት ወይም ለሌላ ግብይት ያላዋለው ከሆነ የታክሱ ባለሥልጣን እነዚህ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ታክስ ለሚከፈልበት ግብይት እስከሚውሉ ድረስ ታክስ ለሚከፈልበት ግብይት እንደዋሉ አድርጎ ሊወስድ አይችልም፡፡

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

4. የተመዘገበው ሰው ታክስ ለሚከፈልባቸው ግብይቶች የዋሉ ወይም የሚውሉ ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን የገዛ እንደሆነ የታክስ ማስታወቂያ ከሚቀርብበት የሂሳብ ጊዜ በፊት ታክስ ለሚከፈልበት ግብይት ያልዋሉ ቢሆንም በአዋጁ አንቀጽ 21 በተመለከተው የሂሳብ ጊዜ ውስጥ የታክስ ተቀናሽ እንዲደረግለት ሊጠይቅ ይችላል::

5. ታክስ ለሚከፈልበት ግብይት ባልዋሉት ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ላይ የተጠየቀው የታክስ ተቀናሽ ከተሰበሰበው ታክስ በላይ በመሆኑ ምክንያት በአዋጁ አንቀጽ 27 መሠረት ታክስ ከፋዩ ተመላሽ ማግኘት የሚችል ከሆነ፣ የተመላሽ ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል:: ሆኖም የታክሱ ባለሥልጣን የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያውን እና የተመላሽ ጥያቄውን ከመረመረ እና ትክክለኛነታቸውን ካረጋገጠ በኋላ ታክስ ከፋዩ እነዚህን ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ታክስ ለሚከፈልበት ግብይት ማዋል ሲጀምር የታክስ ተቀናሽ እንዲደረግለት ሊፈቅድ ይችላል::

## 18. በገዥው ስለሚሰበሰብ ታክስ

በኢትዮጵያ ነዋሪ ካልሆነና ለተጨማሪ እሴት ታክስ ካልተመዘገበ ሰው አገልግሎት የሚያገኝ እና በአዋጁ አንቀት 23 መሠረት የተጨማሪ እሴት ታክሱን ገቢ ማድረግ ያለበት ሰው ወይም ድርጅት ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ቅፅ ላይ የተመለከቱትን መረጃዎች ሞልቶ ለታክሱ ባለሥልጣን ማቅረብ አለበት::

## 19. የዲፕሎማቲክ አቋም ያላቸው ድርጅቶች የታክስ ተመላሽ

1. የዲፕሎማቲክ አቋም ያላቸው ድርጅቶች ለሥራቸው ማስፈፀሚያ ከአገር ውስጥ በሚገዟቸው ዕቃዎች ሊከፈል የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ የከፈሉበትን ማስረጃ ሲያቀርቡ ታክሱ ተመላሽ ይደረጋል::

Democratic ... Ministry of Revenue

F1298

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተፈቀደው የታክስ ተመላሽ ተጠቃሚ ስመሆን የሚፈልጉ የዲፕሎማቲክ አቋም ያላቸው ድርጅቶች የታክሱ ባለሥልጣን በሚወስነው ጊዜ እና በሚያዘጋጀው ቅድ የተመላሽ ጥያቄ ያቸውን ማቅረብ እና ጥያቄ ያቸውን የሚደግፉ መረጃዎችን ማቅረብ አለባቸው::

## 20. የሃይማኖት ድርጅቶች ተነጣጥለው የሚመዘገቡበት ሁኔታ

1. የሃይማኖት ድርጅት ከአምልኮት ጋር በተያያዘ ከሚሰጠው አገልግሎት ውጪ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ታክስ የሚከፈልባቸው ግብይቶችን የሚያካሂድ ከሆነ ስተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ ያለበት መሆኑ የሚወሰነው ታክስ የሚከፈልበት ጠቅላላ እንቅስቃሴው ተደምሮ ነው::

2. የሃይማኖት ድርጅቱ በሚያከናውነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ላይ ሊከፈል የሚገባውን ታክስ በአንድነት አስልቶ በእያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ አንድ የታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ የሚያስቸግረው መሆኑን የታክሱ ባለሥልጣን የተረዳ እንደሆነ የሃይማኖት ድርጅቱ የተለያዩ ቅርንጫፎች በተናጠል እንዲመዘገቡ ሊያደርግ ይችላል::

3. ስተጨማሪ እሴት ታክስ የመመዝገብ ግዴታ ያለበት የሃይማኖት ድርጅት በሥሩ ያሉት የልማት ተቋሞች ወይም ተመሳሳይ አገልግሎት የሚሰጡ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ቅርንጫፎቹ ተነጣጥለው እንዲመዘገቡ ስባለሥልጣኑ ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል:: ባለሥልጣኑ በዚህ ዓይነት ስተናጠል ምዝገባ የሚቀርበውን ጥያቄ ስመቀበል ወይም ሳስመቀበል ሙሉ ሥልጣን አለው::

4. የሃይማኖት ድርጅቱ ቅርንጫፎቹ በተናጠል እንዲመዘገቡ ያቀረበውን ጥያቄ ባለሥልጣኑ የተቀበለው ወይም ባለሥልጣኑ በራሱ ተነሳሽነት የሃይማኖት ድርጅቱ የልማት ድርጅቶች ወይም ተመሳሳይ ተግባር ያላቸው አንድ ወይም ከአንድ በላይ ቅርንጫፎች በተናጠል እንዲመዘገቡ ያደረገ እንደሆነ፣ የተናጠል ምዝገባ የሚከናወነው ባለሥልጣኑ ተገቢ ነው ብሎ የሚያምንበትን ሁኔታ እና ገደብ መሠረት በማድረግ ይሆናል::

294

21. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከ 25 ታኅሣ 1997 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ______ ቀን 1997 ዓ.ም

Federal Democratic Republic Ministry of Revenues

ጌታቸው በላይ
የገቢዎች ሚኒስትር